# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት**

*የካቲት 2009 ዓ.ም*

*አዲስ አበባ*

# ማውጫ


**ማውጫ** ........................................................................................................................I

**ማጠቃለያ (EXECUTIVE SUMMARY):-** ...............................................................................I

**ክፍል አንድ** ....................................................................................................................1

መግቢያ ..............................................................................................................................1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት ..............................................................................................2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ፣ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ ሥልጣንና ተግባር.....................................................2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ መዋቅርና የሰው ኃይል.................................................................................6

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........................................................................................7

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ፤...........................................................................................................8

የኦዲት አካባቢ (AUDIT AREA) ..........................................................................................8

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ እና የመመዘኛ መስፈርት ......................................................................8

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ.................................................................................................................9

የዳልጋ ከብት የዝርያ ማሻሻል የሥራ ፍሰት መግለጫ .....................................................................10

(PROCESS DESCRIPTION) ...........................................................................................10

**ክፍል ሁለት፣**.....................................................................................................................11

**ግኝቶች**.............................................................................................................................11

2.1. የተሻለ የእንስሳት ዝርያና የዘር ሀብትን ለመለየት እና ለመምረጥ የሚያስችል ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ፡-.................................................................11

ዝርያ ማሻሻያ ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ እና እስትራቴጂ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡- ..........11

የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዓመታዊ እቅድ አዘገጃጀትን በተመለከተ፡-........................11

የእንስሳት የርቢ፣ የመረጣ፣ የብዜት፣ የአጠቃቀምና የጥበቃ ፕሮግራም መዘጋጀቱን በተመለከተ፣ ..........12

የእንስሳት የዝርያና የዘር፣ የጥራትና የምርታማነት ብሔራዊ ደረጃና የመለያ ባህሪ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ..........13

ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን የምርመራ መስፈርቶች ትግበራ እና የኳራንታይን አገልግሎትን በተመለከተ፡-..........14

አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በመሆን የምርምር ሥራ መከናወኑን በተመለከተ፡-15

2.2. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲጠበቁ ስለመደረጉ፡-16

ለዝርያ ማሻሻል ለሚመረጡ እንስሳት የጤና አገልግሎት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡- ..... 16

ነባርና ዘራቸው እየመነመነ ያሉ የእንስሳት ዝርያዎች መጠበቃቸውን በተመለከተ፡-. 18

ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች ላይ ጥናት ስለመደረጉ እና መረጃ አያያዙን በተመለከተ፣ ..... 19

የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ ጥገና እና ስርጭትን በተመለከተ፡-..... 20

የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ሥርጭትን በተመለከተ፡-..... 22

በድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነትን በተመለከተ፡-..... 23

2.3. የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መባዛታቸውን፣ መሰራጨታቸውን እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ስለመደረጉ፡-..... 26

የእንስሳት የብዜትና የስርጭት ማዕከላት መቋቋማቸውን በተመለከተ፡- ..... 26

የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ሥርጭትን በተመለከተ፡- ..... 27

የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያን አስመልክቶ የእውቀት፣ የክህሎትና የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱን በተመለከተ፡-..... 28

ክፍል ሦስት፣..... 29

መደምደሚያ ..... 29

ክፍል አራት..... 32

የማሻሻያ ሀሳብ፤ ..... 32

አባሪ ሁለት ፡የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር ተቋማዊ ቁመና (ORGANOGRAM) ..... 39

አባሪ ሦስት፡ በየአመቱ ያሉ የእንስሳትን ሞትና የመኖ ፍጆታ..... 40

አባሪ አራት፡ ..... 41

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ወላይታ ዞን እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ በዓመት ውስጥ ..... 41

ለማቅረብ የታቀደ፣ የቀረበ እና ጥቅም ላይ የዋለ አባላዘር ብዛት፡-..... 41

አባሪ አምስት ..... 42

በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ በድራት ማጎልበቻ (ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ ላሞች ........ 42

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ በድራት ማጎልበቻ (ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ ላሞች ........ 42

አባሪ ስድሰት ........ 43

በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ የፈሳሽ ናይትሮጂን የጥገና ወጪ ........ 43

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ የፈሳሽ ናይትሮጂን ........ 43

የጥገና ወጪ ........ 43

አባሪ 7፡ በናሙና የታዩ ቦታዎች፣ ማዕከላትና ቢሮዎች ........ 44

## ማጠቃለያ (Executive summary):-

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸም፣ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና እንደዚሁም ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር ላ የክዋኔ ኦዲት አካሂዷል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2009 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ኦዲቱ በዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸም ላይ የተከናወነ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ ያሸፈነው የሶስት በጀት ዓመታትን ከ2006- 2008 ዓ.ም እና የ2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን በማካተት ነው፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ዝርያ ማሻሻያ ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ እና እስትራቴጂ አለመዘጋጀቱ፣
- አርሶ አደሩ የተሻለ ዘር ለማግኘት ሲል በተደጋጋሚ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን የሚያስጠቃ ቢሆንም እንስሳቶቹ እርግዝና ሊይዙ ባለመቻላቸው በወረዳ ደረጃ የተዳቀሉ እና በድራት ማጎልበቻ ሆርሞን አማካኝነት የተዳቀሉ እንስሳቶች ውጤታማነት አነስተኛ መሆኑ፣
- ከውጪ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት ዝርያዎች (ለዘር በቁም፣ በአባላዘር፣ በሽል ወይም በማንኛውም መልኩ) በሚገቡበት ጊዜ በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲሁም ፍተሻ ተደርጎባቸው እንዲገቡ አለመደረጉ እና ወደ ሀገር የሚገቡትም ሆነ ከሀገር ውስጥ የሚሰበሰቡትም እንስሳት ላይ የሚሰጠው የኳራንቲን አገልግሎት ደካማ መሆኑ፣
- የዝርያ ማሻሻል ሥራን ለማከናወን ከኔዘርላንድ ከገቡት 300 ክበድ ላሞች ውስጥ በበሽታ ምክንያት እስከ ጥቅምት 16/2009 ዓ.ም ድረስ በህይወት ያሉት 34 ብቻ መሆናቸው፣
- የሰበታ የእንስሳት የጤና ላቦራቶሪ በሪፖርት ቁ.322/16 በ16/09/16 በተጻፈ በሆለታ አስኳል የእናቶች መንጋ ማዕከል ለሚገኙ 220 እንስሳት ላይ ምርመራ አድርጎ ሁሉም በመተንፈሻ አካል በሽታ (IBR) የተጠቁ መሆናቸው ያረጋገጠ ሲሆን የመተንፈሻ አካል በሽታ በዘር የሚተላለፍ መሆኑ እየታወቀ ኮርማ ከነዚህ ዝርያዎች እንዲመረጥ እና ዘሩ እንዲሰራጭ መደረጉ፣
- በሆለታ አስኳል የእናቶች መንጋ ከ2005-2009 የተወለዱ እንስሳት ብዛት 196 የሞቱ ደግሞ ከ2005-2009 በቁጥር 667 መሆኑ፣

- ሚ/ር መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ ተቀናጅቶ የማይሰራ መሆኑ፣
- አባላዘርን ለማስቀመጥ የሚረዳ የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽኖች ብልሽት ሲያጋጥማቸው በወቅቱ ተጠግነው ወደ ሥራ እንዲገቡ የማይደረግ እና የፈሳሽ ናይትሮጅን እጥረት መኖሩ እና ማምረቻ ማሽኑ በከፍተኛ ወጪ ያለ ጨረታ እንዲጠገን የተደረገ መሆኑ፣
- በየክልሉ ከ2006 ዓ.ምና ከዚያ በፊት የነበሩ የእንስሳት ዝርያን የሚያሻሽሉ፣ የሚያባዙና ይጠብቁ ማዕከላት ወደ ግሉ ዘርፍ የተዘዋወሩ ቢሆንም ከእንስሳት ዝርያ ጋር የተያያዘ ሥራን የማያከናውኑ እና በሌላ ሥራ ላይ የተሰማሩ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ የማያገኙ ከሆነ የአገሪቱ የእንስሳት ዝርያ እና ዘሮች ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡ መሆኑን በኦዲቱ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ሚ/ር መ/ቤቱ ዝርያ ማሻሻያ ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ እና እስትራቴጂ አዘጋጅቶ መተግበር አለበት፡፡
- በተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች የተዳቀሉ እንስሳቶች ውጤታማነትን በመገምገምና ግብረ መልስ በመስጠት ውጤታማ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ከውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ ለዝርያ ማሻሻያ በሚመረጡ እንስሳቶች ላይ አስፈላጊው የኳራንታይን አገልግሎትና የጤና ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ ተቀናጅቶ መስራት አለበት፡፡
- የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽኖች ብልሽት ሲያጋጥማቸው በወቅቱ ተጠግነው ወደ ሥራ እንዲገቡ እና የፈሳሽ ናይትሮጅን በበቂ ሁኔታ ሊቀርብ ይገባል፡፡
- የእንስሳት ዝርያን የሚያሻሽሉ፣ የሚያባዙና የሚጠብቁ ማዕከላት በአመቺ እና በአስፈላጊ ቦታዎች ሊስፋፉና ሊቋቋሙ ይገባል፡፡

  የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብታቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚታወቁ አገሮች አንዷ ስትሆን በአፍሪካ አንደኛ ደረጃ በዓለም 10ኛ ደረጃን በመያዝ እምቅ የእንስሳት ሀብት ባለቤት መሆኗ ይታወቃል፡፡

2. እንስሳት ለተለያዩ የልማት አገልግሎቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ በግብርናው የአመራረት ስርዓት ዘርፍ ውስጥ 6 ሚሊዮን የሚደርሱ የእርሻ በሬዎች፣ 8 ሚሊዮን የሚሆኑ የጋማ ከብትና ግመል ለመጓጓዣነት፣ የቁም እንስሳት ውጤቶችና ተዋፅኦዎች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝባቸው የልማት ዋና ምንጭ ናቸው፡፡

3. የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት በማገልገል፣ የውጪ ምንዛሬ በማስገኘት እና የውጪ ምርቶችን በመተካት ረገድ ከፍተኛ ሀገራዊ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን ከእንስሳት ሀብታችን ተገቢውን ጠቀሜታ ለማግኘትና ምርትና ምርታማነትን በአግባቡ ማሳደግ እንዳይቻል እንቅፋት ከሆኑት ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ ባህላዊ የእንስሳት አረባብ ዘዴ፣ የመኖ በብዛትና በጥራት ያለመኖር፣ በቂ የእንስሳት ጤና አገልግሎት አለመሟላት እና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት አለመኖር ናቸው፡፡

4. በመሆኑም የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ይቻል ዘንድ በሀገራችን የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች የጀነቲክ ቁስ መጠበቅ፣ ማሻሻል እና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

5. ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተሻለ ዝርያን ከውጭ በማስገባት የማሻሻሉ ሥራ በሀገራችን የሚበረታታ ቢሆንም ለዝርያና ለዘር ማሻሻያ አገልግሎት የርቢ እንስሳት በተለያየ መልኩ ከውጭ ሲገቡም ሆነ ከገቡ በኋላ አስፈላጊው ጥንቃቄ ካልተደረገ በስተቀር በሀገራችን የእንስሳት ዝርያ ላይ የሚያስከትለው የዝርያ መበረዝና መሸርሸር እንዲሁም ሌሎች አሉታዊ ተጽዕኖዎች ከወዲሁ ግምት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም የሀገር ውስጥ የእንስሳት ዝርያዎች በልቅ የረቢ ሂደት ምክንያት ተፈላጊ ባህሪያቸው እየተሸረሸረ እና እየተበረዘ ንጹህ የሀገር እንስሳት ዝርያ እንዳይጠፋ አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

6. ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙም የእንስሳቱን ዝርያና ዘሮች ምርታማነት በማሳደግ የህብረተሰቡን ማህበራዊ ኑሮና የሀገሪቷን ገቢ ማሳደግ

የሚቻል ሲሆን  መንግስት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት በግብርና ሚኒስቴር ስር በማውጣት እነዚህን ተግባራት ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚ/ር በ2008 ዓ.ም እንዲቋቋም ተድርጓል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት

7. ከእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ጋር በተያያዘ ለመጀመሪያ ጊዜ የእርሻ መሥሪያ ቤት በሚል መጠሪያ በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት በ1900 ዓ.ም የተቋቋመ መሥሪያ ቤት ሲሆን በተለያዩ መጠሪያዎች ሲጠራ ቆይቶ በ2003 ዓ.ም በግብርና ሚኒስቴር በእንሰሳት ሀብት ዘርፍ ስር የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያን የሚከታተል የስራ ክፍል ተቋቁሞ እስከ 2007 ዓ.ም ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በ2008 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር በአዲስ መልክ ሲዋቀር የዝርያ ማሻሻያ ልማትን በተመለከተ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር አዲስ ለተቋቋመው የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተዘዋውሯል፡፡

8. በተጨማሪም መንግሥት ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ዘርፍ ትኩረት በመስጠት ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ሲሰራ የቆየውን የሆለታ አስኳል መንጋ የዝርያ ማሻሻያ እንዲሁም ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የነበረውን የቃሊቲ የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከላት ተጠሪነታቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዝርያ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እንዲሆን አድርጓል ፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ፣ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ ሥልጣንና ተግባር

**ራዕይ፡-**

9. በ2017 ዘመናዊ የእንስሳት ኢንዱስትሪ በመገንባት ሀገራችን በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ፣ በአፍሪካ ቀዳሚና ተመራጭ የእንስሳት ሀብት ምርት አቅራቢ እንድትሆን ማድረግ፡፡

**ተልዕኮ፡-**

10. የእንስሳትና ዓሣ እምቅ ሀብትና የዘመናዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ህብረተሰብ በመገንባትና በገበያ የሚመራ የእንስሳት ሀብት ልማት በማስፋፋት፣ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ የሚውል አቅርቦትን በማሳደግ፣ የህብረተሰቡን የተመጣጠነ ምግብና መሰረተ ሰፊ ለአየር ንብረት ለውጥ  የማይበገር

የኢኮኖሚ ዕድገት በማረጋገጥ እና መካከለኛ ገቢ ያለው ህብረተሰብ በመገንባት ሂደት ውስጥ የእንስሳት ሀብት ዘርፍ ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡

11. ዝርያን በማሻሻል የእንስሳት መኖን በጥራትና በብዛት በማምረት የእንስሳት በሽታዎችን በመከላከልና በመቆጣጠር ለእንስሳት ሀብት ልማት የሚውል የግብዓት አቅርቦትና የእንስሳትና ዓሣ ምርት ግብይት በማሳደግ ሀገራችን ከዘርፉ የላቀ ተጠቃሚ እንደትሆን በዘርፉ ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶችን የመደገፍና ኢንቨስመንት እንዲስፋፉ እገዛ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡

**እሴቶች፡-**

12. የሚኒስቴር መ/ቤቱ እሴቶች

- የማያቋርጥ አዎንታዊ የለውጥ ባህል፣
- ለስኬት ተግባር ዕውቅና መስጠት፣
- ለላቀ ውጤት በጋራ መሥራትና መደጋገፍ፣
- ለመልካም አስተዳደር መርሆዎች መገዛት፣
- በውስን ሀብት የላቀ ውጤት ማስመዝገብ፣
- ለህዝብ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት ፣
- የሴቶችና ወጣቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

ናቸው፡፡

**ስልጣንና ተግባር፡-**

13. በአዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

- የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ዘርፍን ምርታማነት ለማሻሻል ለአርሶ አደሩ፣ ለአርብቶ አደሩ፣ ለግል ባለሀብቱ እና በከተማ እንስሳት ልማት ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጡ የኤክስቴንሽንና የስልጠና አገልግሎቶችን ያስፋፋል፡፡
- ለገበያ የሚቀርብ ማንኛውንም እንስሳት፣ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያሰችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
- ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት የግብዓት አቅርቦት፣ ስርጭትና ግብይት አቅምን በመገንባት አስተማማኝ አቅርቦትን ያረጋግጣል፡፡ የጥራት ቁጥጥርን ስርዓት የዘረጋል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

- የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሥርዓቶች ይዘረጋል፡፡
- ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት እንስሳትና ዓሣ ላይ የኳራንታይን አገልግሎት ይሰጣል፡፡ተላላፊ የእንስሳት በሽታዎችና በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ ተህዋስያን ተጽዕኖዎችን ይከላከላል፡፡
- የእንስሳትና የዓሣ እንዲሁም የእንስሳና ዓሣ ተዋጽኦ ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡
- የእንስሳት መድኃኒቶች እና መኖ ጥራት እንዲሁም የእንስሳት ህክምና አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፡፡ የእንስሳትና የዓሣ ሀብት ልማት ምርምሮች ባለድርሻ በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
- በአርብቶ አደር አካባቢ ለእንስሳት ሀብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ ውኃ፣ መሰረተ ልማትና የመኖ ባንኮች መስፋፋታቸውን ይከታተላል፤ የተፈጥሮ እና የመስኖ ግጦሽ መሬት ልማት እና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፤ አገራዊ መረጃ ያደራጃል፡፡
- የዓሣ ምርትና አቅርቦትን ያስፋፋል፡፡
- በዓሣ ልማት ዘርፍ ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብትና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡
- በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ህጎች ድንጋጌዎች የእንስሳትና ዓሣ ሀብትን በሚመለከት ለግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

**የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት፡-**

14. ከላይ የተጠቀሱትን በአዋጅ ለሚ/ር መ/ቤቱ የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶችን ለማስፈጸም ሚ/ር መ/ቤቱ ከዋቀራቸው ዳይሬክቶሬቶች አንዱ የዝርያ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ሲሆን የዳይሬክቶሬቱ ተግባርና ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡
    - ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት የሚውሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ምርታማነትና ቀጣይነት ያለው ለውጤታማነት የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን እንዲሁም አግባብነት ያላቸዉ የፈጻሚ ተቋማት ማቋቋሚያ ኃሳብ ያመነጫል፣

- የሀገሪቱ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች እንዲለዩ፣ እንዲባዙ፣ እንዲጠበቁና ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ብሔራዊ የርቢ፣ የብዜት፣ የአጠቃቀምና ጥበቃ ስትራቴጂና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣
- እንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች የላቀ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ዒላማ ያደረገ የልየታ፣ የመረጣ፣ የብዜትና የአጠቃቀም ሥርዓት መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የምርታማነት መገምገሚያ መስፈርቶችን ይቀይሳል፣
- በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የዝርያና ዘሮች ልቀትና ሥርጭት እንዲፈቀድ ያደረጋል፣
- የርቢ እንስሳት፣ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች እንዲጠበቁ፣ እንዲባዙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችሉ የብዜትና የሥርጭት ማዕከላት በአስፈላጊና አመቺ አካባቢዎች እንዲቋቋሙ፣ ዉጤቱም ለተጠቃሚ ህብረተሰብ በአግባቡ እንዲዳረስ ለማድረግ፣ አሠራሩም በሕጋዊ አፈጻጸም የተደገፈ እንዲሆን ሀሳብና ስትራቴጂ ያመነጫል፣
- የሀገሪቱን የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች የማሻሻያ፣ የአጠቃቀምና የጥበቃ ሥራ የተሟላ መረጃዎች የሚያዙበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው ጋር እንዲደራጁ ያደርጋል፣ ለሀገሪቱ ተጠቃሚዎችና አግባብነት ላላቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚተላፍበትን በጋራ ስልት ይነድፋል፣ ሲፈቀድም በየደረጃው የመልእክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች በመጠቀም በድረገጽ እንዲሰራጩ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን በመከታተል የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፣
- በእንስሳት ዝርያዎችና ዘር ብዜትና ሥርጭት የልማት ሥራዎች ውስጥ በአቅምና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የግል ባለሀብቶች፣ የሴቶች እና የወጣቶች ልማት ቡድኖች፣ የህብረት ሥራ ማህበራት ወደ ልማቱና ብዜት ተግባራት ስለሚገቡበት ስልትና ስትራቴጂ አግባብነት ካላቸዉ አካላት ጋር ያጠናል፣ አማራጭ አሠራሮችንም ያመነጫል፣
- ምርምር የሚሹ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች በተሻለ ልማት ጥቅም ላይ ስለሚውሉበት ስልት በመለየት በሳይንሳዊ ምርምርና የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲያገኙ አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በቅንጅትና በትብብር ይቀይሳል፤
- የአየር ንብረት ለውጥ በመቋቋም መኖርና መራባት እንዲሁም ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ ሀገር በቀል የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች በልዩ ክብካቤ፣ ጥብቅ ሥፍራዎች ተይዘው እንዲራቡ፣ እንዲጠበቁና ከአረንጓዴ የኢኮኖሚ

ስትራቴጂው ጋር በማጣጣም ጥቅም እንዲሰጡ የሚያደርግ ስልት ከሚመለከታቸው ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመሆን አግባብነት ያለው አሠራር ይቀይሳል፣

- ለርቢ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች፣ የዝርያና የዘር ጥራትና የምርታማነት ደረጃዎች፣ መለያ ባህሪያት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ብሔራዊ ደረጃዎችንና የመለያ ባህሪያት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣
- ምርጥና የተሻለ ምርታማነት ያላቸው የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን ወደ ሀገር በማስገባት የዝርያ፣ ዘሮች ማሻሻያ ለማካሄድ ለሀገሪቱ የተለያዩ የአካባቢ ሁኔታና የአረባብ ሥርዓቶች የተሻሉና ተመራጭ ስለመሆናቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያጠናል፣
- የዶሮ፣ የወተትና የሥጋ እንስሳት፣ የንብና የሐር ትል ብዜትና ሥርጭት ማዕከላትን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ የተገኘውን ውጤት ይገመግማል፣ ግብረመልስ ይሰጣል፣ ለበላይ አመራር አካል ሪፖርት ያደርጋል፣
- በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ፣ አጠቃቀምና ጥበቃ ላይ በእንስሳት ሀብት ልማት ለተሠማሩ ባለሀብቶች፣ ቡድኖችና የሕብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም ለዳይሬክቶሬቱ ባለሙያዎች የዕውቀትና ክህሎት የአቅም ግንባታ፣ የአጭርና የረጅም ጊዜ ትምህርት እንዲስፋፋ፣ የተሻለ አሠራር ይቀይሳል፣
- ብሔራዊ የዝርያ ማሻሻያ ፕሮራሞችንና ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በበላይነት ይቀይሳል፣

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ መዋቅርና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

15. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአንድ ሚኒስትርና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች የሚመራ ሲሆን፣ ለሚኒስትሩ ቀጥታ ተጠሪ የሆኑ 12 ዳይሬክቶሬቶች፣ በልማትና ግብይት ዘርፍ ሥር 10 እና በጤናና መኖ ቁጥጥር ዘርፍ ሥር 6 ዳይሬክቶሬቶች በድምሩ 28 ዳይሬክቶሬቶች ሲኖሩት የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ተጠሪነቱ ለልማትና ግብይት ዘርፍ ነው፡፡ በተጨማሪም አምስት ለሚ/ር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት አሉ፡፡ (ድርጅዊ መዋቅሩ በአባሪ 2 ተያይዟል)

### የሰው ኃይል

16. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዚያ ወር 2008 ዓ.ም ከቀረበው ማስረጃ ለማወቅ

እንደተቻለው 57 (18.56%) ሴት ሰራተኞች፣ 250 (81.4%) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 307 የቋሚ ሰራተኞች እና 18 ኮንትራት ሰራተኞች ያሉት ሲሆን የቋሚ ሰራተኞች የሰው ኃይል ባላቸው የሙያ ደረጃ ሲተነተን ፒኤችዲ 1 (0.3%)፣ የመጀመሪያ ዶክትሬት ዲግሪ(DVM) 43 (14.00%)፣ ሁለተኛ ዲግሪ 29 (9.44%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 73 (23.78%)፣ ዲፕሎማ 38 (12.38%) እና ከዲፕሎማ በታች ያሉ 123 (40.06%) ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

17. የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግሥት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2006-2008 ዓ.ም ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጭ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡ በ 2008 ዓ.ም የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር እየተጠቀመ ያለው ከግብርና ሚኒስቴር ጋር እያለ ለዘርፉ ከተመደበለት የ2008 በጀት በማዘዋወር መሆኑ ታውቋል፡፡ የ2008 ዓ.ም በጀት አፈጻጸም እስከ ሰኔ ወር ድረስ በስራ ላይ የዋለን የሚያመለክት ነው፡፡

| ዓ.ም | የተመደበ በጀት | | ጠቅላላ የተመደበ በጀት | ጥቅም ላይ የዋለ | | ጥቅም ላይ የዋለ ጠቅላላ ወጪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መደበኛ | ካፒታል | | መደበኛ | ካፒታል | በብር | በፐርሰንት |
| 2006 | 632,071,741.16 | 222,688,860.00 | 854,760,601.16 | 518,298,546.58 | 211,057,817.67 | 729,356,364.25 | 85% |
| 2007 | 1,242,332,349.24 | 251,747,100.00 | 1,494,079,449.24 | 1,241,206,422.12 | 209,106,623.11 | 1,450,313,045.23 | 97% |
| 2008 | 235,526,386.30 | 119,954,194.80 | 355,480,581.11 | 199,108,742.70 | 80,480,394.07 | 279,589,137.77 | 78.7% |
| 2009 | 101,622,874.00 | 89,593,410.00 | 191,216,284.00 | 22,428,966.70 | 24,886,802.00 | 47,315,769.07 *እስከ 30/04/09 ድረስ ብቻ* | 24.7% |

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ፤

18. የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸም፣ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና እንደዚሁም ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (audit area)

19. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ Audit Area) "የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ስኬታማ በሆነ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን እና ለዚሁ ተግባር የዋለው ግብአት ያስገኘውን ተመጣጣኝ ውጤት (Value for Money) ለማረጋገጥ ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ እና የመመዘኛ መስፈርት

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

20. በተለየው የኦዲት ካባቢ (Potential audit area) ስር ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (audit issues) ተለይተዋል እነሱም፡-

1. ሀገራዊ የእንስሳት ዝርያና የዘር ሀብትን ለመለየት፤ለመምረጥ፤ ለማሻሻል የሚያሰችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣
2. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች እንዲጠበቁ መደረጉን ማረጋገጥ፣.
3. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች መባዛታቸውን፣ መሰራጨታቸውን እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረጉን ማረጋገጥ፤

የሚሉት ናቸው፡፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፣

21. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ለመገምገም የሚያስችል 32 የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ተዘጋጅቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተልኳል፡፡ (የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡)

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

22. የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2009 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው የሶስት በጀት ዓመታትን ከ2006- 2008 ዓ.ም እና የ2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

23. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ሲሆን የኦዲት ቡድኑ የሚኒስቴር መ/ቤቱን አሠራር የሚመለከቱ የተለያዩ አዋጆች፣ ሠነዶችና ማስረጃዎችን (የተለያዩ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የጥናት ሪፖርቶች፣ የየአመቱን ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ የስትራቴጅክ ዕቅድ)፣ የሥራ አመራር (የማናጅመንት) ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱን በሚመለከት የወጡ የተለያዩ ብሮሸሮች ጋዜጦችና የተለያዩ መመሪያዎችን የከለሰ ሲሆን፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በቃሊቲ ብሔራዊ ሰው ሰራሽ ዘዴ ማራቢያ ማዕከል፣ በሆለታ የኮርማ እናቶች መንጋ (እርባታ) ማዕከላት፣ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን የመስክ ምልከታ በማድረግ ለሥራ ኃላፊዎችም መጠይቅ አቅርቧል፡፡

24. በተጨማሪም በናሙና በተመረጡ ሁለት ክልሎች (ኦሮሚያና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች)ና በሥራቸው ያሉ የተመረጡ ወረዳዎች፣ የእንስሳት ዓሣ ሀብት ቢሮዎች እንዲሁም የእርባታ ማዕከላት፣ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የፈሳሽ ናይትሮጂን ማማረቻ ማዕከላት እና የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪ ማዕከል በመገኘት የመስክ ጉብኝት በማድረግና ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች መጠይቅ በማቅረብና የተለያዩ ሰነዶችን በመከለስ እና አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በመገምገም የተከናወነ ነው፡፡ (ዝርዝር የታዩ የክልል፣ ዞንና ወረዳዎች በአባሪ 7 ተይዟል፡፡)

## የዳልጋ ከብት የዝርያ ማሻሻል የሥራ ፍሰት መግለጫ

## (process description)

25. የዝርያ ማሻሻያ ሥራን የሚከናወንበት የአሰራር ፍሰት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርቧል፤

- ተፈላጊ የእንስሳት ዝርያ በምርምር መለየት፣
- በምርምር የተለዩትና ዝርያዎች መመዝገብ፣
- የተመዘገቡትን ለቀጣይ ዘር ምንጭነት ኮርማና ጊደር ማፍራት፣
- የአስኳል መንጋ ማጠናከሪያ ዝርያ(ኮርማ) አባላዘር ከውጭ ማስገባት፣
- የተመረጡ ኮርማዎች ብቃት ግምገማ ማካሄድ፣
- ብቃት ያላቸውን ኮርማዎች መንከባከብ፣
- ብቃት የሌላቸውን ማስወገድ፣
- ጥራቱን የጠበቀ አባለዘር ማምረትና ማከማቸት፣
- የበሽታ ቁጥጥርና የአባለዘር ጥራት ክትትል ማድረግ፣
- ናይትሮጂን ማምረትና ማሰራጨት.
- የመስክ ማዳቀል ተግባራትን በአረቢው ፍላጎት ማከናወን፣
- የአቅም ግንባታ ስልጠና ማካሄድ፣

ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፣

## ግኝቶች

### 2.1. የተሻለ የእንስሳት ዝርያና የዘር ሀብትን ለመለየት እና ለመምረጥ የሚያስችል ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ፡-

**ዝርያ ማሻሻያ ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ እና እስትራቴጂ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-**

26. በአገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑ የእንስሳት የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች የሚመሩበት እና ሊደረስበት የታሰበውን አቅጣጫ የሚያመላክት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በናሙና ተመርጠው በታዩ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የክልል (የኦሮሚያና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች)ና ዞንና ወረዳዎች እንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤት ለመረዳት እንደተቻለው የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል የሚያስችል ፖሊሲ (ስትራቴጂ) ተቀርጾ በስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ ታውቋል፡፡

28. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የርቢ ፖሊሲ ረቂቅ ተዘጋጅቶ የሚመለከተው አካል አይቶት እንዲጸብርና እንዲጎለብት መስከረም 2008 ቀርቧል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን መስከረም 2008 ዓ.ም የተዘጋጀው ረቂቅ የሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ሰጥተውበት አስካሁን እንዲጸድቅ ያልተደረገበትን ምክንያት በተመለከተ ምላሽ አልሰጡም፡፡

29. የአገሪቱን እንስሳት ዝርያን ለማሻሻል የሚረዳ ፖሊሲ እና እስትራቴጂ ባለመኖሩ እስካሁን የተሰሩ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ስራዎች እንዳይቀናጁና ወጥ በሆነ ሁኔታ እንዳይተገበሩ ብሎም ሀገራችን በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ፣ በአፍሪካ ቀዳሚና ተመራጭ የእንስሳት ሀብት ምርት አቅራቢ እንዳትሆን ያደርጋል፡፡

**የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዓመታዊ እቅድ አዘገጃጀትን በተመለከተ፡-**

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን ለማከናወን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና

በመተንተን አገር አቀፍ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዓመታዊ ዕቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፤

31. በሚኒስቴር መ/ቤቱ (የቀድሞው የግብርና ሚኒስቴርን ጨምሮ) ከ 2006 -2008 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ አመታዊ የእንስሳት የዝርያ ማሻሻያ ዕቅድ የሚዘጋጅ ቢሆንም የሚዘጋጀው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዕቅድ የአርብቶ አደሩ፣ የከፊል አርብቶና የአርሶ አደሩን የእንስሳት ዝርያ ፍላጎት ላይ የዳሰሳ ጥናት በማከናወንና የእንስሳት ዝርያ ፍላጎትን በማሰባሰብ እንደማይዘጋጅ ታውቋል፡፡ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላቱም ዕቅድ የሚያዘጋጁት ማዕከላዊ እስታትስቲክስ የሚያወጣውን የእንስሳት ብዛት መግለጫን መሰረት በማድረግ እንጂ ከአርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩ እንዲሁም የግል ባለሀብቶችን የዝርያ ፍላጎት የሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብ የማያቅዱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የክልል፣ ዞንና ወረዳ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤት በተደረገ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባዘጋጁት የዓመት እቅድ ላይ ከክልል ባለሙያዎች ጋር የጋራ ምክክር መድረክ በማዘጋጀት ውይይት ተደርጎበት የጋራ እቅድ በማድረግ ወደ ሥራ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዋነኛ ተጠቃሚ የሆኑትን የአርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩን የእንስሳት ዝርያ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የዳሰሳ ጥናትና ትንበያን ያላካተተ እቅድ የተሟላ እቅድ ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

33. የተጠቃሚዎቹን ፍላጎት ለማወቅ የሚያግዝ የዳሰሳ ጥናት፣ ግምገማና ትንበያ ሳይኖር የተዘጋጀ እቅድ ዝርያዎችና ዘሮችን በሀገሪቱ ለሚገኙ አርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደርና አርብቶ አደር በሚፈለገው አይነት፣ መጠን፣ ጥራትና ወቅትን ጠብቆ ለማሰራጨትና ለመተግበር አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**የእንስሳት የርቢ፣ የመረጣ፣ የብዜት፣ የአጠቃቀምና የጥበቃ ፕሮግራም መዘጋጀቱን በተመለከተ፣**

34. አገር አቀፍ የእንስሳት የርቢ፣የመረጣ፣ የብዜት፣ የአጠቃቀምና የጥበቃ ፕሮግራም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዝርያ ማሻሻያ ሥራን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (የእንስሳትና ዓሳ ኃብት ሚ/ር ሥር የሚገኙ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የፌዴራልና የክልል ግብርና ምርምር ማዕከላት፣ የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ የእንስሳት መደኃኒትና መኖ ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ ሌሎች የግልና የመንግሥት እንስሳት እርባታ ማዕከላት) ጋር በመቀናጀት ፕሮግራሙ እንደማይዘጋጅ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ የክልል፣ ዞን እና ወረዳ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮዎች/ መምሪያዎች/ጽ/ቤቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለመረዳት ተችሏል፡፡

36. የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የርቢ፣ የመረጣና አጠቃቀምን የሚያግዝ አምስት ፓኬጅ በማዘጋጀት የሚመለከታቸውን የክልል ባለሙያዎች ሀሳብ እንዲሰጡበትና እንዲያዳብሩ ተደርጎ ዝግጅቱ የተጠናቀቀ ስለሆነ በቀጣይ ለክልሎች እንዲሰራጭ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

37. የዝርያ ማሻሻያ ሥራን የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እንዲዘጋጅ አለመደረጉ፣ የሚከናወኑ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ እና የተቀናጀ እንዳይሆን እና ባለድርሻ አካላትም ትኩረት ሰጥተው በባለቤትነት እንዳይሰሩ በማድረግ ውጤታማነቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።

***የእንስሳት የዝርያና የዘር፣ የጥራትና የምርታማነት ብሔራዊ ደረጃና የመለያ ባህሪ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤***

38. የዝርያና የዘር፣ የጥራትና የምርታማነት ብሔራዊ ደረጃና የመለያ ባህሪ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የዝርያና የዘር፣ የጥራትና የምርታማነት ብሔራዊ ደረጃና የመለያ ባህሪ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ መዋል እንዳለበት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቋማዊ አደረጃጀት አጠቃላይ መግለጫ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም ሥርዓቱ አልተዘጋጀም፡፡የዝርያና የዘር፣ የጥራትና የምርታማነት ብሔራዊ ደረጃና የመለያ ባህሪ አስጣጥን አስመልክቶ መመሪያ (guide line) ቢዘጋጅም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

40. የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ሰፊ ሥራን የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

(ኤ.ቲ.ኤ) ጋር በዚህ ዓመት ሥራውን ለመተግበር እንቅስቃሴ እንደተጀመረ ገልጸዋል፡፡

41. ደረጃና የመለያ ባህሪ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመሆኑ እንስሳት ዝርያ ማሻሻል፤ የርቢ፤ የመረጣ፤ የመጠቀምና ፤የመጠበቅ ሥራው እንደዚሁም የምርት መጠን እንዲቀንስና የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነት እንዲቀንስ በማድረግ ብሎም እንስሳቱ እንዲጠፉ ያደርጋል።

**ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን የምርመራ መስፈርቶች ትግበራ እና የኳራንታይን አገልግሎትን በተመለከተ፡-**

42. ከውጪ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት ዝርያዎች (ለዘር በቁም፣ በአባላዘር፣ በሽል ወይም በማንኛውም መልኩ) በሚገቡበት ጊዜ በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲሁም ፍተሻ ተደርጎባቸው እንዲገቡ እና ወደ ሀገር የሚገቡትም ሆነ ከሀገር ውስጥ የሚሰበሰቡትም እንስሳት ላይ የኳራንቲን አገልግሎት በመስጠት አስፈላጊው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

43. ማናኛውም ከውጪ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት ዝርያዎች (ለዘር በቁም፣ በአባላዘር፣ በሽል ወይም በማንኛውም መልኩ) ወደ አገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ የዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን 6 የምርመራ መስፈርቶች (Bovine Tuberculosis, Brucellosis, Bovine viral diarrhea-mucosa disease (BVD-MD), Bovine Venereal Trichomoniasis, Infectious Bovine Rhinotrachitis (IBR), and Campylobacter fetus) እንዲያሚሉና በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው (GUIDELINES FOR IMPORT AND EXPORT ANIMAL AND ANIMAL GENETIC MATERIAL) መግባት እንዳለባቸው በግልጽ ተቀምጧል፡፡

44. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የዝርያ ማሻሻል ሥራን ለማከናወን ከኔዘርላንድ ሀገር በ2005 ዓ.ም ለገቡት 300 ክበድ ላሞች

- የተሰጠው ሰርተፍኬት የእንስሳቱን የጤና ሁኔታ የማይገልጽ መሆኑን፣
- ክበድ ላሞቹ ሲገቡ ከ3 እስከ 7 ወራት እርግዝና የነበራቸው ቢሆንም ከውጭ ሀገር ገብተው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በሽታ ምልክት ያሳዩ እና ውርጃ የታየባቸው መሆኑን

በአጠቃላይ 300 ክበድ ላሞቹም ሆነ ሌሎች ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከአገር ውስጥ በሚሰበሰቡት እንስሳት ላይ የኳራንቲን

አገልግሎት በመስጠት ተላላፊ የእንስሳት በሽታዎችና በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ ተህዋስያን ወደሌሎቹ በመተላለፍ ተጽዕኖዎች እንዳይፈጠሩና ያሉትም ዝርያዎች እንዳይጠፉ የሚደረገው የመከላከል ሥራ አነስተኛ መሆኑ፣ የኳረንቲን ሥራውም በተቀናጀና ለአገልገሎቱ በሚያስፈልጉ ግብአቶች የተሟሉ አለመሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በየማዕከላቱ በተደረገ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

45. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አልሰጡም፡፡

46. በተቀመጠው የኳረንቲን መስፈርት መሰረት ከውጭ ለሚገቡ የእንስሳት ዝርያዎች የተሟላ ምርመራ ለእንስሳቱ ያለመደረጉ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ስራ ለታለመለት ግብና ዓላማ ከመዋል ይልቅ ከፍተኛ የሆነ የሀብት ብክነት እንዲኖር እና አገሪቱ የነበራት የእንስሳት ዝርያዎች እንዲጠፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በመሆን የምርምር ሥራ መከናወኑን በተመለከተ፡-**

47. ዝርያዎችና ዘሮችን በመለየት አገሪቱ ያላትን የእንስሳት ዝርያዎችን ለማሻሻልና የአገሪቱን የእንስሳት ሀብት በአይነት፣ በጥራትና በብዛት ለማሳደግ የሚረዳ ዝርያዎች በሳይንሳዊ ምርምር ውጤት እንዲገኝ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብነት ካላቸው የምርምር ተቋማት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ ተቀናጅቶ የማይሰራ መሆኑን፣ ከእነዚህ ተቋማት ዝርያ ማሻሻያን አስመልክቶ የሚወጡ የምርምር ውጤቶች ሚ/ር መ/ቤቱ በሥሩ ለሚያስተዳድረው የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት እንዲደርስ እና የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ውስጥም ስለሚያጋጥሙ ምርምር የሚሹ ችግሮችን ለግብርና ምርምርና ኢኒስቲትዩት እና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማሳወቅ የምርምር ተግባራት እንዲከናወንባቸው አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

49. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ከምርምር ተቋማት ጋር የመስራት ጅምር

እንዳለና የተመራማሪዎችን የቴክኖሎጂ ግኝቶች ለሰራተኛውና ለተጠቃሚው ለማድረስ መረጃ የሚለዋወጡበት ስርዓት አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

50. ምርምር የሚሹ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች በመለየት በሳይንሳዊ ምርምር ውጤት እንዲያገኙ ባለመደረጉ የሚመረጡት ወይም የሚሻሻሉት የእንስሳት ዝርያ ዓይነቶች እና ጥቅም ላይ የሚዉሉት የዝርያ ማሻሻያ ዘዴዎች ውስን እንዲሆኑና በዝርያ ዙሪያ ምርምር የሚሹ ችግሮች በአፋጣኝ እንዳይፈቱ ከማድረጉም በላይ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ተመራማሪዎች እና በተለያየ ደረጃ ተመርቀው የሚወጡ የዘርፉ ባለሙያዎች ችግር ፈች ምርምር ላይ የድርሻቸውን እንዳይወጡ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በአገር ውስጥ እውቀት የተገኙ ውጤቶች ውጤታማ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተደጋገመ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች እንዲኖሩ በማድረግ የሀገሪቱ ውስን ሀብት ለብክነት እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡

## 2.2. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲጠበቁ ስለመደረጉ፡-

**ለዝርያ ማሻሻል ለሚመረጡ እንስሳት የጤና አገልግሎት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-**

51. ለዝርያ ማሻሻል የሚመረጡ እንስሳት ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል፣ የስጋት ትንተና ለማካሄድና መጠኑን ለመለየት፣ በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ የዝርያ ማሻሻል ሥራን ለማከናወን ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም

- በ2005 ዓ.ም ከኔዘርላንድ ከገቡት 300 ክበድ ላሞች ውስጥ በበሽታ ምክንያት እስከ ጥቅምት 16/2009 ዓ.ም ድረስ በህይወት ያሉት 34 ብቻ መሆናቸው፣
- የሰበታ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ በሪፖርት ቁ.322/16 በ16/09/16 በተጻፈ በሆለታ አስኳል የእናቶች መንጋ ማዕከል ለሚገኙ 220 እንስሳት ላይ ምርመራ አድርጎ ሁሉም በመተንፈሻ አካል በሽታ (IBR) የተጠቁ መሆናቸው ያረጋገጠ ሲሆን በመተንፈሻ አካል (IBR) በሽታ የተጠቁ እንስሳቶች በዘር (genetic) አማካኝነት በሽታን እንደሚያስተላልፉ የሰበታ የእንስሳት የጤና ላቦራቶሪ በ ቁ.322/16 በ16/09/16 በተጻፈ ሪፖርት ቢያሳውቅም ችግራቸው እየታወቀ ከነዚህ ላሞች


የተወለደ ኮርማ ለዝርያ ማሻሻያ ሥራ ከሆለታ አስኳል መንጋ ማዕከል ተመርጦ በቃሊቲ ዝርያ ማሻሻያ ማዕከል ዘሩ ለተጠቃሚው እንዲሰራጭ መደረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

53. የአገሪቱን የእንስሳት ዝርያዎች ለመጠበቅና በሽታን ለመከላከል በወቅቱ እርምጃ እየተወሰደ እንዳልሆነ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ የክልል፣ ዞን እና ወረዳ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡ በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ውስጥ ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ የእንስሳት ጤና ሁኔታዎች ሲከሰቱ የስጋት ትንተና በማካሄድና መጠኑን በመለየት ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች በተከሰተባቸው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ቦታዎች (ክልሎች) በመገኘት ስለደረሰው ጉዳት እና መንስኤ ጥናት በማድረግ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ አለማድረጉ፣

54. በብሄራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ማዕከል እና በሆለታ አሰኳል መንጋ የእናቶች ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ውስጥ ለዝርያ ማሻሻል ተግባር ተይዘው የሚገኙ የወተት ላሞች፣ ኮርማዎች እና ጥጆች በክትባት መደኃኒት አቅርቦት እጥረት እንዲሁም የምርመራ ባለሙያ አቅም ውስንነት ምክንያት በተደጋጋሚ በቆዳ ጉርብርብ፣ ቲቢ፣ የጡት በሽታ በመጠቃት ለሞት የተዳረጉ መሆኑ ለዝርያ ማሻሻያ የሚቀርቡት አንዳንድ የክትባት መደኃኒቶች ውጤታማ አለመሆናቸውን ለማዕከላቱ ከቀረቡ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ለዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት የቀረበ የቆዳ ጉርብርብ ክትባት ለአመት ያገለግላል ተብሎ ለእንስሳቱ ቢሰጥም በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱ አብቅቶ /Fail አድርጎ/ እንስሳቱ በበሽታው ምክንያት የሞቱ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዝርዝር መረጃው የእንስሳቱን የሞት ብዛት እንደሚከተለው በቻርት ቀርቧል፡፡ (ዝርዝር ሰንጠረዡ **በአባሪ 3** ተያይዟል፡፡)




*ማስታወሻ*

- **ከ2006 ዓ.ም እና 2008 ዓ.ም የውርጃ ህክምና ቢሰጥም ዝርዝር መረጃው በትክክል ባለመገለፁ፣ መድኃኒቱ ባለመገዛቱ ፣ ላሞቹ በመተንፈሻ አካል በሽታ በመያዛቸው የሰውነት መቋቋም ችግርና የውርጃ ዳታው ከ50% በታች መሆኑ በባለሙያዎቹ ከመገለጹ በስተቀር በትክክል በቁጥር ተለይቶ ባለመያዙ መረጃውን ማካተት አልተቻለም፡፡**
- **የሞቱት ቁጥር ከ2005 ዓ.ም ውጭ ያሉት ነባሮቹን እና አዲስ የተወለዱትን ይጨምራል፡፡**

55. በተለያየ መልኩ ለዝርያ ማሻሻል አገልግሎት እንስሳት ከውጭ ሲገቡም ሆነ ከገቡ በኋላ አስፈላጊው ጥንቃቄ ካልተደረገ በእንስሳቱ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ እና የህብረተሰቡንም ሆነ የሀገሪቷን ገቢ የሚያሳጣ እና የሀገሪቷን እንስሳት ለሞት በመዳረግ ዝርያዎቹ እንዲጠፉ ያደርጋል፡፡

**ነባርና ዘራቸው እየመነመነ ያሉ የእንስሳት ዝርያዎች መጠበቃቸውን በተመለከተ፡-**

56. ነባር እና አዳዲስ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በልዩ ክብካቤ፣ ጥብቅ ስፍራዎች ተይዘው እንዲራቡ እንዲጠበቁና ጥቅም እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

57. ይሁን እንጂ ሚ/ር መ/ቤቱ በወተት ዳልጋ ከብት ላይ ብቻ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን የሚያከናውን ቢሆንም

    - የሀገር ውስጥ ዝርያ የሆኑት የሸኮ ና አቢጋር ዝርያዎች እየተባዙ ባለመሆናቸው ዝርያዎቹ ወደ መጥፋት ደረጃ እየተቃረቡ መሆኑ፣

- በዳልጋ ከብት ላይ በሀገር ውስጥ የቦረና፣ የበጋይት፣ የፎገራ፣ የሆሮ፣ የሸኮና አቢጋር ዝርያዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለዩ ቢሆንም እነዚህን ዝርያዎች በመጠበቅና በማባዛት ማሰራጨት አለመቻሉ፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

58. በተጨማሪ በማዕከል ደረጃ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከዳልጋ ከብት ውጪ በሌሎች የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ በሚችሉ ፍየል፣ በግ፣ የሥጋ ዳልጋ ከብት፣ ፈረስ ወ.ዘ.ተ. ላይ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች እንዲከናወኑ አለመደረጉ፣ የሀገር ውስጥ ዝርያን በማሻሻል ሌሎች ሀገራት ከደረሱበት በማድረስ (Export standard) የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት አለመቻሉን፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው በክልል የሚገኙ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤቶች እንዲሁም በሚ/ር መ/ቤቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

59. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የዝርያ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት አዲስ የተቋቋመ ስለሆነ እየተመናመኑ ስለሚገኙት እንስሳት መረጃ በተሟላ መልኩ እንደሌላቸው እና ከብዝኃ ህይወት ኢንስቲትዩት መረጃዎችን የማሰባሰብ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

60. ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ነባር ዝርያዎችን ለመጠበቅ ዘላቂ የሆነ መፍትሄ እንዲገኝ ካልተደረገ በአገሪቱ ነባር ዝርያዎች እየተመናመኑ እንዲጠፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

**ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች ላይ ጥናት ስለመደረጉ እና መረጃ አያያዙን በተመለከተ፣**

61. ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች ሲከሰቱ በሽታዎቹ በተከሰተባቸው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላትና ቦታዎች (ክልሎች) በመገኘት ስለደረሰው ጉዳት እና መንስኤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የመከላከል ሥራ፣ ጥናት፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግና ስለአጋጠሙ የበሽታ ክስተት ዝርዝር መረጃው በሀገራዊ የመረጃ ቋት ሊይዝ ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ

- በሥሩ በሚገኙ የዝርያ ማሻሻያ ማዕካላት ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች ሲከሰቱ በሽታው እንዳይስፋፋ ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ በቦታው በመገኘት ስለተከሰተው በሽታ ጥናት የማያደርግ መሆኑ፣
- የክትትልና የቁጥጥር ሥራውም በስልክ በሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ብቻ መሆኑ ለዚህም ተብሎ የተዘረጋ ሥርዓት አለመኖሩ፣
- በሆሎታ አስኳል የእናቶች መንጋ ማዕከል ከ2005 ጀምሮ በተከሰተ የእንስሳት የጤና ችግር ላይ እስካሁን ድረስ መፍትሄ ያልተሰጠ መሆኑ፣ እንዲሁም
- ከእንስሳት ዝርያ ጋር በተያያዘ የበሽታ ክስተት ሲያጋጥም የበሽታው ክስተት የሚጠናቀርበት ሀገራዊ የመረጃ ቋት በማቋቋም እንዲያዝ አለመደረጉ፣
- እንስሳቱ ላይ የሚታየውን የበሽታ ዓይነት ለመመዝገብ የሚያስችል ሥርዓት በየማዕከሉ አለመኖሩን፣

በኦዲት ወቅት ለሚመለከታቸው አካላት ከቀረበ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት ተጠይቀው የጤና አገልግሎትን በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት ቢኖርም በእርባታው ውስጥ የተከሰተው በሽታ መድኃኒት የሌለው በመሆኑ እና እንስሳቶቹ የመቋቋም አቅም የሌላቸው በመሆኑ ብዙ እንስሳት ሊሞቱ መቻላቸውን እንዲሁም ለወደፊት ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

64. በሽታው እንደተከሰተ ወቅታዊና አፋጣኝ እርምጃ ካልተወሰደ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከሉ በውስጡ የያዛቸው እንስሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ በሞት እንዲጠቁ በማድረግ ማዕከላቱን አስከመዘጋት የሚያደርሱ እና በሽታውም ከዝርያ ማሻሻያው ማዕከል አልፎ በሀገር ደረጃ በመስራጨት ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል፡፡ በተጨማሪም የተከሰቱት በሽታዎች መቼ፣ የት እና በምን ምክንያት እንደተከሰቱ፣ ያደረሱት ጉዳት እና የተወሰደ እርምጃ የሚያሳይ መረጃ እየተሰበሰበሰ አገራዊ ቋት በማዘጋጀት አለመያዙ ለፖሊሲ ውሳኔዎችም ሆነ ለምርምር ሥራ የሚሆን መረጃ በቀላሉ ማግኘት እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

**የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ ጥገና እና ስርጭትን በተመለከተ፡-**

65. ለዝርያ ማሻሻያ የተመረቱ አባላዘሮችን ለማስቀመጥ የሚጠቅም የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻዎችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች መደበኛ የጥገና ፕሮግራም (Service)

በማዘጋጀት በፕሮግራሙ መሰረት እንዲከናወን እና የፈሳሽ ናይትሮጂኑ ምርት በተጠቃሚዎች ፍላጎት መሰረት እንዲሰራጭ ሊደረግ ይገባል፡፡

66. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- የፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትና ሥርጭት የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ክልሎች በዓመት በታቀደው መጠን መሰረት ማግኘት አለመቻላቸውን በናሙና የታዩ ተጠቃሚዎች የገለጹ መሆኑ፣
- አገሪቱ ውስጥ የሚገኙት የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽኖች ብልሽት ሲያጋጥማቸው በወቅቱ ተጠግነው ወደ ሥራ እንዲገቡ የማይደረግ መሆኑን፣
- ለዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት የሚውል የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻዎችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ማንዋሉ በሚያዘው መሰረት (8000 ሰዓት ከሰራ በኋላ) መደበኛ ጥገና (service) የማይደረግላቸው መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

67. እንዲሁም በተደጋጋሚ የማምረቻ ማሽን ብልሽት የሚደርስባቸው ስለሆነ መሳሪያዎቹን ለመጠገን በናሙና ከታዩት ክልሎች ያለውድድር ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከ2006-2008 ባለው ጊዜ ሁሉንም በክልሉ የሚገኙና በናሙና በታዩት የናይትሮጅን ማምረቻ ማዕከላትን ፍቼ፣ ሻሸመኔ እና ነቀምት ለሚገኙ ማዕከላት ብር 2,935,859 (ሁለት ሚሊየን ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አምስት ሺ ሰምንት መቶ ሀምሣ ዘጠኝ ብር) የደቡብ ህዝቦችና ብሔር ብሔረሰቦች በሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በ2008 ዓ.ም ብቻ ብር 6,657,688 (ስድስት ሚሊየን ስድስት መቶ ሀምሣ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ሰማንያ ስምንት ብር) በድምሩ ብር 9,593,547 (ዘጠኝ ሚሊየን አምስት መቶ ዘጠና ሦስት ሺ አምስት መቶ አርባ ሰባት ብር) ወጪ ተደርጎ እንዲጠገን መደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ ማዕከላት፣ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የክልልና ወረዳ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤት ጋር በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡(ዝርዝር ወጪዎቹ በአባሪው 6 ተያይዟል፡፡)

68. አገሪቱ ውስጥ ለሚገኘው የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽን የጥገና አገልግሎት የሚሰጠው በአንድ ብቸኛ ባለሙያ መሆኑን፣ የፈሳሽ ናይትሮጂን የማምረቻ ማሽን የመለዋወጫ እቃ እጥረት መኖሩን፣ ማሽኑንም በብቸኛነት የሚያቀርበው በአገሪቱ

አንድ ድርጅት ብቻ መሆኑ ችግር መፍጠሩን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት በሀገሪቱ ውስጥ 22 የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽኖች ያሉ ቢሆንም ከዚህ ውስጥ ግማሾቹ ረጅም ጊዜ ያገለገሉ በመሆናቸው በተደጋጋሚ ለብልሽት የሚጋለጡ መሆኑን እና በሀገር ውስጥም ያለው የጥገና አቅም አነስተኛ በመሆኑ ይህን ለማሻሻል በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

70. ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ የሚውል ዘርን ለማቆየት አስፈላጊ የሆነው ፈሳሽ ናይትሮጂን በበቂ ሁኔታ ያለመመረት፣ ማምረቻ መሳሪያዎቹም ሲበላሹ በፍጥነት ተጠግነው ሥራ ላይ ካልዋሉ በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት የሚገኝ ዘር በሚፈለገው መጠን ተሰራጭቶ ውጤት ማምጣት እንዳይቻል የሚያደረግ እና አገሪቱም ከእንስሳት ሀብት የምታገኘውን ጥቅም እንዳታገኝ ያደርጋል፡፡

**የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ሥርጭትን በተመለከተ፡-**

71. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ለአርብቶ አደሩ፣ ለአርሶ አደሩ እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ሊሰራጩ ይገባል፡፡

72. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እንደ ግብዓት የሚሆኑ ኮርማዎችን የሚያዘጋጀው የሆሎታ አስኳል መንጋ የእናቶች ዝርያ ማሻሻያ ማዕከል ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ለዝርያ ማሻሻል የሚመረጡ ኮርማዎችን ማከፋፈል አለመቻሉ፣ በብሄራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ማዕከልም ከ2006-2008 ዓ.ም. ድረስ 5,360,000 አባላዘር ለማምረት ታቅዶ በዚሁ ከላይ በተገለጸው 3 ዓመታት ውስጥ የተመረተው አባላዘር ብዛት 2,422,616 (45%) ብቻ መሆኑ፣
- የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ለአርብቶ አደሩ፣ ለአርሶ አደሩ እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች በወቅቱና በጠየቁት መጠን እንዲደርሳቸው እንደማይደረግ

በናሙና በታዩ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ፣ የክልል፣ ዞንና ወረዳ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤት ከቀረበ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

73. በናሙና በታዩ ወረዳዎች የሚከናወኑ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች (Artificial Insimination Services) ሲሰሩ የዘር እጥረት በመኖሩ ላሞቹ ፍላጎት ባሳዩ ጊዜ

ወቅቱ ተጠብቆ ዘር እንዲሰጣቸው ባለመደረጉ ላሞቹ እርግዝና ሊይዙ አለመቻላቸው በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የክልል ዞንና ወረዳ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤት ከቀረበ መጠይቅና ከተከለስ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ለማሳያ ያህል፡-

በብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል በዓመቱ ውስጥ የተመረተና ለክልሎች የተሰራጨ አባላዘር ብዛት ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| | በዓመቱ ውስጥ ለማምረት የታቀደ የአባላዘር ብዛት በዶዝ | በዓመቱ ውስጥ የተመረተ የአባላዘር ብዛት በዶዝ | በዓመቱ ውስጥ ለክልል የተሰራጨ የአባላዘር ብዛት በዶዝ | የዓመቱ ክንውን ከዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2006 | 1,500,000 | 758,243 | 975,705 | 50.5 |
| 2007 | 2,000,000 | 921,932 | 922,389 | 46 |
| 2008 | 1,860,000 | 742,441 | 790,441 | 40 |
| ድምር | 5,360,000 | 2,422,616 | 2,688,535 | 45.5 |

መግለጫ፡ የተሰራጨው በአመቱ ከተመረተው የበለጠው ከነበረው ክምችት የሚሰራጨውን ስለሚጨምር ነው፡፡

74. ስለጉዳዩ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል የሚመለከታቸው የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ አሁን ያሉት የብዜት ማዕከላት ጥቂት በመሆናቸው ለተጠቃሚው በሚፈልገው መጠን ማቅረብ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ ባሉት የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላትም ሥራው በተገቢው እየተከናወነ ስላልሆነ ይህንን የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

75. በሀገሪቱ በተለያዩ የአየር ጸባይ እና በምርታማነታቸው እንደዚሁም በሌሎች ምክንያቶች አጥጋቢ የሆኑ እንስሳትን ዘር በማሻሻል የማይሰራጭ ከሆነ ሀገሪቱ በእንስሳት ሀብት እስካሁን ይዛ የነበረውን ደረጃ እንድታጣ እና ወደፊትም ልታስመዘግብ ያቀደቻውን እንዳታሳካ ያደርጋታል፡፡

**በድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነትን በተመለከተ፡-**


76. በእንስሳት ዝርያ የማሻሻል ሥራ የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) በመጠቀም የተዳቀሉ እንስሳት ጤናማ ጥጃና ጊደር በመውለድ ውጤታማ እንዲሆኑ ሊደረግና ውጤታቸውም በየጊዜው ሊገመገም ይገባል፡፡

77. የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነትን በተመለከተ በየጊዜው ግምገማ እየተከናወነ የግምገማ ሪፖርት የሚቀርብ ቢሆንም በቀረበው የግምገማ ሪፖርት መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ አይሰጥም፡፡ አብዛኛው የድራት ማኅልበቻ ሆርሞን በመጠቀም በአርሶ አደሩ/ አርብቶ አደሩ የተዳቀሉ እንስሳት ውጤት ወደ እርግዝና መሸጋገራቸውን እና ጤናማ ጥጃ/ጊደር መውለዳቸውን በየማዕከሉ መረጃው ተጠናቅሮ አይያዝም፡፡ በህብረተሰቡ ዘንድም በሆርሞኖች ስርጭት ምክንያት የተገኘውን ለውጥ ለማወቅ ጥናት የማይደረግ በመሆኑ ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡


78. በተጨማሪም በናሙና በተመረጡ የክልል፣ የዞንና ወረዳ ቢሮዎች እና የእርባታ ማዕከላት ከሰጡት መልስ አብዛኛው የድራት ማኅልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤት (የተዳቀሉ እንስሳት ወደ እርግዝና መለወጥ) አነስተኛ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በተደረገ የመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

79. በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት እና በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ በድራት ማኅልበቻ (ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ ላሞች ውጤታማ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ቻርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ዝርዝሩም በአባሪ 5 ተያይዟል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ማሳያ:-



የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት ማሳያ፡-




80. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት በሲንክሮናይዜሽን እንስሳትን የማዳቀሉ ሥራዎች በዘመቻ የሚሰሩ በመሆኑ ለቀረቡ እንስሳቶች ሁሉ ሆርሞን የሚሰጥ መሆኑን እና ዘር የማመንጫ አካላቸውን መርምሮ የማየት ችሎታ ባለመኖሩ የተፈጠረ መሆኑን ገልጸው ችግሮቹን ለመፍታት እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡

81. የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) በመጠቀም የሚዳቀሉ እንስሳት ያስገኙት ውጤት ተገምግሞ ጉድለትም ካለ ማስተካከያ የማይደረግ ከሆነ ዘሩን ለማግኘት፣ እንስሳቱን ለማሰባሰብ፣ ሆርሞኑን ለመግዛት፣ አዳቃይ ቴክኒሺያኖችን ለማብቃት የወጣው ወጪና ጊዜ እንዲባክን ከማድረጉም በተጨማሪ በማዳቀሉ ሊገኝ የሚችለው የተሻሻለ የእንስሳት ዝርያን ለማግኘት እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ የዝርያ መሻሻያ ፕሮግራሙ በአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና ሌሎች ተጠቃሚዎች በኩል እምነት የማይጣልበት ተቀባይነት የሌለው እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## 2.3. የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መባዛታቸውን፣ መሰራጨታቸውን እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ስለመደረጉ፡-

**የእንስሳት የብዜትና የስርጭት ማዕከላት መቋቋማቸውን በተመለከተ፡-**

82. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ለማከናወን ማዕከላት ለዋነኛ ተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግን ታሳቢ አድርጎ በአመቺ አካባቢዎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል ባለድርሻ አካላት ጋር በመናበብ ሊቋቋሙ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የማዕከላቱን የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ

- የእንስሳት የብዜትና የስርጭት ማዕከል ለአብዛኛው ተጠቃሚዎች አመቺ በሆኑ አካባቢዎች ያልተቋቋሙ መሆኑ፣
- በየክልሉ ከ2006 ዓ.ምና ከዚያ በፊት በመንግስት ይተዳደሩ የነበሩ እና የእንስሳት ዝርያን የሚያሻሽሉ፣ የሚያባዙና የሚጠብቁ ማዕከላት (ሀበርኖሳ፣ ጎቤ፣ አንዳሳ፣ ፣ ዲዳ ጥያራ፣ በጌ፣ አኖ …) ወደ ግሉ ዘርፍ ከተዘዋወሩ በኋላ ከእንስሳት ዝርያ ጋር የተያያዘ ሥራን የማያከናውኑና በሌላ ሥራ ላይ የተሰማሩ መሆኑ፣
- በግልም ሆነ በመንግሥት ሥር የሚገኙ ዝርያን በማሻሻልና በመጠበቅ ሥራ ላይ የተሰማሩ በክልል የሚገኙትን ተቋማት የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ግብረ መልስ እንዲሰጥ አለመደረጉን፣
- ከ2006 ዓ.ም በፊት ጊደሮች እና ኮርማን ለተጠቃሚዎች ያሰራጩ የነበሩ የመንግሥትና የግል ማዕከላት ሥርጭት ያቆሙ መሆኑን
- እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዝርያን በማባዛት ሊያሰራጩ የሚችሉ (የግል ወይም የመንግሥት) ማዕከላትን እንዲቋቋም አለመደረጉን

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የክልል የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ጽ/ቤቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. ይህ ጉዳይ የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ለግለሰብ ተዛውረው ለሌላ አገልግሎት ስለዋሉት የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ምክንያቱን ለማወቅ መረጃ የማሰባሰብ ስራ እየተሰራ መሆኑን እና

በአመቺ አካባቢም ሌሎች ማዕከላትን ለማቋቋም እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

85. የሀገሪቱን የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች በበቂ እና በተገቢው በማምረት እና ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ለማግኝትና ዝርያዎቹን እንዲጠቀሙ ካልተደረገ ከዘርፉ አርብቶ ቸደሩ፣ አርሶ አደሩ እንዲሁም አገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝ ያደርጋታል፡፡ በተጨማሪም የአገሪቱን የእንስሳት ሀብት እየቀነሰ በእንስሳት ሀብት የነበራትን ገጽታም እንዲቀየር የሚያደርግ ይሆናል፡፡

**የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ሥርጭትን በተመለከተ፡-**

86. የአገሪቱን የእንስሳት ሀብት፣ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ለሚገኙ ተጠቃሚዎች ዘመናዊ የመረጃ ማሰራጫ ዘዴዎችን በመጠቀም (በድህረ ገጽ) ሊያስተዋውቅና ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ በሀገሪቱ የሚገኙ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ለተለያዩ ተጠቃሚዎች የሚተዋወቅበትና የሚሰራጭበት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት (ድህረ ገጽ፣ ኢ ሜል..) ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ከክልል እንስሳትና ዓሳ ሃብት ጽ/ቤቶች እና ከምርምር ተቋማት የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከተ መረጃዎችን ለማግኘት እንደሚቸገሩ ታውቋል፡፡

88. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ይህንን ሥራ የሚሰራ ክፍሉ በማቋቋም ላይ እንዳለና አሁን መ/ቤቱ እየተጠቀመበት ያለው የመረጃ ማስተላለፊያ መንገድ ከፌዴራል እስከ ቀበሌ ባለው የመ/ቤቱ አደረጃጀት በመጠቀም መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ከፌዴራል እስከ ቀበሌ ካለው አደረጃጀት ውጭ ያሉ የአገር ውስጥ ተጠቃሚዎችም ሆነ ከአገር ውጭ ያሉ መረጃዎች እንዴት መረጃ እያገኙ እንደሆነ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

89. የእንስሳት ሀብት፣ ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች በቀላሉ ተጠቃሚዎች በዘርፉ ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈልጉ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች በመረጃ ላይ የተደገፈ ውሳኔ እንዳይወስኑ በማድረግ አገሪቱ ከእንስሳት ሀብት ዘርፍ መገኘት ያለበት ጥቅም እንዳይገኝ ያደርጋል፡፡ ለምርምር ሥራ ለሚፈልጉትም

በተገቢው መረጃ ላይ የተመሰረተ ምርምር እንዳያደርጉ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

***የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያን አስመልክቶ የእውቀት፣ የክህሎትና የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱን በተመለከተ፡-***

90. በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አጠቃቀምና ጥበቃ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች፣ ቡድኖች፣ የህብረተሰብ ክፍሎች የእውቀትና፣ የክህሎትና የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡

91. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዘርፍን ምርታማነት ለማሻሻል የኤክስቴንሽንና የሥልጠና አገልግሎቶችን ማስፋፋት እንዳለበት በሚኒስቴር መ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጅ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም የአዳቃይ ቴክኒሺያን ስልጠና እንጂ የተለያዩ የእንስሳት ዝርያዎችን በመጠበቅና በመጠቀም ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች፣ ቡድኖችና የህብረተሰብ ክፍሎች የእንስሳት ዝርያ ማሻሻልን አስመልክቶ የእውቀት፣ የክህሎትና የአቅም ግንባታ ስልጠና እና ግንዛቤ እንዲያገኙ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የክልል የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ጽ/ቤቶች እና በሚ/ር መ/ቤቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

92. በኦዲቱ ወቅት የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ኃላፊዎች ስለሁኔታው ለቀረበላቸው መጠይቅ ሲመልሱ በአውደ ጥናት ወቅት ስለዝርያ ማሻሻልና የእንስሳት ርቢ ለአርቢዎችና ለባለሀብቶች ገለጻ እንደሚሰጥ፣ በስፋትና በተደጋጋሚ ለማድረግም የአቅም ውስንነት መኖሩን፣ ብሮሸሮችና ማንዋሎች በበራሪ ፅሁፎች በየጊዜው እንደሚዘጋጅ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን አገሪቱ ካላት ሰፊ የእንስሳት ሀብትና ተጠቃሚዎቹ በመላው አገሪቱ ከመገኘታቸው አንጻር አልፎ አልፎ የሚደረጉ ውይይቶችና አውደ ጥናቶች ዋነኛ የሀብቱ ተጠቃሚዎችን የማያካትት በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

93. ለአርብቶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩ፣ አርሶ አደሩ፣ ባለሀብቶች፣ ቡድኖች፣ የህብረተሰብ ክፍሎች የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያን በተመለከተ ተደራሽነት ባለው መልኩ በፕሮግራም ስልጠና እንዲያገኙ ካልተደረገ ኋላ ቀር በሆነው እና በልምድ በሚታወቀው መንገድ ብቻ ዝርያውን እና ዘርን ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት ውጤት እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

## ክፍል ሦስት፣

## መደምደሚያ

94. የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን እና የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች ተገኝተዋል፡፡

- የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ያልተቀረጸ መሆኑ፤
- የእንስሳት ዝርያ እቅድ ሲዘጋጅ የአርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩን እና ግል ባለሀብቱን የተሻሻሉ ዝርያዎች ፍላጎትን መሰረት ግንዛቤ ውስጥ ያገባ ዕቅድ የማይዘጋጅ መሆኑ፤
- አገር አቀፍ የእንስሳት የርቢ፣ የመረጣ፣ የብዜት፣ የአጠቃቀምና የጥበቃ ስትራቴጂና ፕሮግራም ሲዘጋጅ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት የማያሳትፍ መሆኑ፣
- የእንስሳት የዝርያና የዘር፣ የጥራትና የምርታማነት ብሔራዊ ደረጃና የመለያ ባህሪ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ እና የተዘጋጀው መመሪያውም ሥራ ላይ አለመዋሉ፣
- ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከአገር ውስጥ በሚሰበሰቡት እንስሳት ላይ የኳራንቲን አገልግሎት በመስጠት ተላላፊ የእንስሳት በሽታዎችና በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ ተህዋስያን ወደሌሎቹ በመተላለፍ ተጽዕኖዎች እንዳይፈጠሩና ያሉትም ዝርያዎች እንዳይጠፉ የሚደረገው የመከላከል ሥራ አነስተኛ መሆኑ፣
- የኳረንቲን በተቀናጀ ሁኔታ የማይከናወን እና ለኳረንቲን አገልገሎቱ በሚያስፈልጉ ግብአቶች የተሟሉ አለመሆናቸው፣
- የዝርያ ማሻሻል ሥራን ለማከናወን ከኔዘርላንድ ሀገር በ2005 ዓ.ም ለገቡት 300 ክበድ ላሞች የዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን 6 የምርመራ መስፈርቶች በሚሟላት በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲሁም ፍተሻ ተደርጎባቸው እንዲገቡ ያልተደረገ መሆኑ፣

- አገሪቱ ያላትን የእንስሳት ዝርያዎችን ለማሻሻልና የአገሪቱን የእንስሳት ሀብት በአይነት፣ በጥራትና በብዛት ለማሳደግ የሚረዳ ዝርያዎች ላይ ከሚመለከታቸው የምርምርና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፣
- በመተንፈሻ አካል (IBR) በሽታ የተጠቁ እንስሳቶች በዘር (genetic) አማካኝነት በሽታን እንደሚያስተላልፉ እየታወቀ ከነዚህ ላሞች የተወለደ ኮርማ ለዝርያ ማሻሻያ ሥራ ዘሩ ለተጠቃሚው እንዲሰራጭ መደረጉ፣
- ነባር በአገር አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲጠበቁና ዘራቸው እንዳይጠፉ አለመደረጉ፤
- ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች በተከሰተባቸው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ቦታዎች (ክልሎች) በመገኘት ስለደረሰው ጉዳት እና መንስኤ ጥናት በማድረግ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ፣
- በዝርያ ማሻሻያ ማእከላት በሚገኙ እንስሳት ላይ ስለሚያጋጥም የበሽታ ክስተት መረጃው ማዕከላዊ የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) እንዲያዝ አለመደረጉ፤
- ለዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት የሚውል የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻዎችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች በማንዋላቸው መሰረት መደበኛ ጥገና (service) እና ሲበላሹም በፍጥነት ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ፣
- የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽን የጥገና አገልግሎት የሚሰጠው በአንድ ብቸኛ ባለሙያ መሆኑን፣
- ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ የተመረጡ አባላዘሮችን ለማስቀመጥ የሚጠቅም የፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትና ሥርጭት የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያላደረገ መሆኑ፤
- ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እንደግብዓት የሚሆኑ ኮርማዎችን የሚያዘጋጀው የሆለታ አስኳል መንጋ የእናቶች ዝርያ ማሻሻያ ማዕከል ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ለዝርያ ማሻሻል የሚመረጡ ኮርማዎችን ማከፋፈል አለመቻሉ፣
- በብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ማዕከል 2006-2008 ዓ.ም. ድረስ 5,360,000 አባላዘር ለማምረት ታቅዶ በዚሁ ከላይ በተገለጸው 3 ዓመታት ውስጥ የተመረተው አባላዘር ብዛት 2,422,616 አፈጻጸሙ ከዕቅዱ 45% ብቻ መሆኑ፤
- የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ለአርብቶ አደሩ፣ ለአርሶ አደሩ እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች በወቅቱና በጠየቁት መጠን እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፤

- በዝርያ ማሻሻል ሥራ የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነት በተመለከተ የሚከናወነው ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ እንዲሰጥ አለመደረጉ፤
- የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤት (የተዳቀሉ እንስሳት ወደ እርግዝና መለወጥና ጥጃ/ ጊደር መውለድ) ዝቅተኛ መሆኑ፤
- በየክልሉ ከ2006 ዓ.ምና ከዚያ በፊት የነበሩ የእንስሳት ዝርያን የሚያሻሽሉ፣ የሚያባዙና ይጠብቁ የነበሩ ማዕከላት ወደ ግሉ ዘርፍ የተዘዋወሩ ማዕከላት ከእንስሳት ዝርያ ጋር የተያያዥ ሥራን የማያከናውኑ መሆኑ፣
- የአገሪቱን የእንስሳት ሀብት፣ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ለሚገኙ ተጠቃሚዎች ዘመናዊ የመረጃ ማሰራጫ ዘዴዎችን በመጠቀም (በድህረ ገጽ) የማይተዋወቁ መሆኑ፣
- በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አጠቃቀምና ጥበቃ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች፣ ቡድኖች፣ የህብረተሰብ ክፍሎች የእውቀትና፣ የክህሎትና የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳብ፤

95. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚከናወነውን የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ፣ በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2017 ዘመናዊ የእንስሳት ኢንዱስትሪ በመገንባት ሀገራችን በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ፣ በአፍሪካ ቀዳሚና ተመራጭ የእንስሳት ሀብት ምርት አቅራቢ እንድትሆን ለማድረግ የያዘውን ራዕይ ዕውን ለማድረግ የአገሪቱ የዝርያ ማሻሻያ ተግባር የሚመራበትና አቅጣጫ በማስያዝ ሥርዓት ባለበት መንገድ ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በማዘጋጀትና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ  አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዓመታዊ  ዕቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በረቂቅ ደረጃ ላይ አለ የተባለው የርቢ ፖሊሲ በተቻለ ፍጥነት የሚመለከታቸው እንዲመክሩበትና እንዲያዳብሩት በማድረግ ጸድቆ ወደ ተግባር ሊሸጋገር ይገባል፡፡
- ❖ አገር አቀፍ የእንስሳት የርቢ፣ የመረጣ፣ የብዜት፣የአጠቃቀምና የጥበቃ ስትራቴጂና ፕሮግራም እና የእንስሳት የዝርያና የዘር፣ የጥራትና የምርታማነት ብሔራዊ ደረጃና የመለያ ባህሪ አሰጣጥ ሥርዓት  የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ ከውጪ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት ዝርያዎች (ለዘር በቁም፣ በአባላዘር፣ በሽል ወይም በማንኛውም መልኩ) በሚገቡበት ጊዜ በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲሁም ፍተሻ ተደርጎባቸው እንዲገቡ ቁጥጥር በማድረግ ወደ አገሪቱ እንዲገቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለኳረንቲን የተሟላ ምርመራ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ግባቶች ተሟልተው አገልግሎቱን በመስጥት ጤናማ ዝርያዎችና ዘሮች ብቻ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም በአገር ውስጥ የተሻለ ውጤት የሚያመጡ ዝርያዎችና ዘሮችን ለመለየትና ጥቅም ላይ ለማዋል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ካሉ የምርምር እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት ሊሰራ ይገባል፡፡

- ለዝርያ ማሻሻል የሚመረጡ እንስሳት ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ፣ ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች በተከሰተባቸው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ቦታዎች (ክልሎች) በመገኘት ስለደረሰው ጉዳት እና መንስኤ ጥናት በማድረግ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡
- በዝርያ ማሻሻያ ማዕከላትና በተሰራጩ ዝርያዎች ምክንያት በሚገኙ እንስሳት ላይ ስለሚያጋጥም የበሽታ ክስተት መረጃው እየተጠናቀረ የሚያዝበት እና ለወደፊት ለፖሊሲ ውሳኔዎች እና የምርምር ሥራዎች በሚያግዝ መልኩ እየተተነተነ በሀገራዊ የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) በማዘጋጀት እንዲያዝ ሊደረግና ተጠቃሚዎች የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በአገሪቱ ያሉ ነባር የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች እየተባዙ የሚሰራጩበት እና ወደ መጥፋት እየተቃረቡ ያለቸውንም ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በልዩ ክብካቤ፣ ጥብቅ ስፍራዎች ተይዘው እንዲራቡ እንዲጠበቁና ጥቅም እንዲሰጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ለማከናወን ማዕከላት ለዋነኛ ተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግን ታሳቢ አድርጎ በአመቺ አካባቢዎች የመንግስት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ማዕከላት እንዲጠናከሩና የግል ማዕከላት በስፋት እንዲቋቋሙ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት የሚውል የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻዎችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች የጥገና ፕሮግራም በማዘጋጀት በፕሮግራሙ መሰረት እንዲጠገን በማድረግ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ለዝርያ ማሻሻያ የተመረቱ አባላዘሮችን ለማስቀመጥ የሚጠቅም የፈሳሽ ናይትሮጂን ምርት እንደዚሁም የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ለአርብቶ አደሩ፣ ለአርሶ አደሩ እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች በሚፈልጉት መጠን እንዲሰራጩ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የፈሳሽ ናይትሮጅን መሳሪያዎችን በብዛት እንዲቀርቡ ለማድረግ ሆነ የተበላሹ የፈሳሽ ናይትሮጅን መሳሪያዎች ጥገና በፍጥነት እንዲከናወን ለማድረግ መሳሪዎቹን በአገር ውስጥ የሚመረቱበት ወይም መንግስት ሌላ አማራጭ የሚፈልግበት ስትራቴጂ በመንደፍ ለሚመለከተው አካል በማስወሰን ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከፍተረኛ ትምህርት ተቋማት እና ከግብርና

የቴክኒክ ኮሌጆች ጋር በመመካከር መሳሪዎቹን የሚጠግኑ ባለሙያዎቹ የሚፈሩበትን መንገድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- ❖ በዝርያ ማሻሻል ሥራ የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነትና፣ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ማዕከላትን የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ በመገምገም የሚመለከታቸው አካላት እርምጃ እንዲወስዱበት ግብረ መልስ ሊሰጥ እና ለተግባራዊነቱም አስፈላጊው ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ❖ የአገሪቱን የእንስሳት ሀብት፣ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ለሚገኙ ተጠቃሚዎች ዘመናዊ የመረጃ ማሰራጫ ዘዴዎችን በመጠቀም (በድህረ ገጽ) የሚተወቁበት መንገድ በማመቻቸት የግል ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ ብሎም ምርቶቹን ለውጭ ገበያ ለመላክ ሁኔታዎቹን ሊያግዝ ይገባል፡፡
- ❖ በአጠቃላይ እንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚ/ር አስመልክቶ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት ለሚያከናውነው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ፣ የተሻለ የእንስሳት ዝርያና የዘር ሀብትን ለመለየት እና ለመምረጥ የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት ጤንነታቸው የተጠበቀ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን በማፍራት፣ በሚፈልጉት መጠን እና እንዲሁም ወቅት የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን እንዲሰራጩ ቢያደርግ አርብቶ አደሩ፣ አርሶ አደሩ እና ሌሎች ተጠቃሚዎች ምርታማና ጥራቱ የተጠበቀ የእንስሳት ዝርያን እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡
- ❖ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዋነኛነት የተቋቋመበትን ዓላማና ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ በማመቻቸት በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ጉዳዩን በማሳወቅ፣ በመከታተልና በመቆጣጠር ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው ፌዴራል መ/ቤቶች፣ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ የሚመለከታቸው በናሙና የታዩ የክልል እና የወረዳ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

### አባሪ -አንድ፡ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት


| **የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ** (Audit Issues) | **የኦዲት መመዘኛ መስፈርት** *(Evaluative Criteria)* |
|---|---|
| **1. የተሻለ የእንስሳት ዝርያና የዘር ሀብትን ለመለየት እና ለመምረጥ የሚያሰችል ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤** | 1. ሚ/ር መ/ቤቱ ዝርያ ማሻሻያ ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ /እስትራቴጂ/ ቀይሶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2. የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል አስፈላጊ መረጃ በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3. ሀገር አቀፍ የእንስሳት የርቢ ፣ የመረጣ፣ የብዜት፣ የአጠቃቀምና የጥበቃ ስትራቴጂና ፕሮግራም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 4. የአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ እና የሌሎች ተጠቃሚዎች የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያ ፍላጎት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ትንበያ በየዓመቱ ተዘጋጅቶ እንዲገመገም ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 5. የእንስሳት የዝርያና የዘር፣ የጥራትና የምርታማነት ብሔራዊ ደረጃና የመለያ ባህሪ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 6. የሀገሪቱ የተሻሉና ምርታማ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች መስፈርት ተዘጋጅቶ እንዲለዩ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 7. ለዝርያ ማሻሻያ የተመረጡ እንስሳትን በእድሜ በጾታና በምርት መጠን ተለይተው እንዲያዙ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 8. ከውጪ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት ዝርያዎች (ለዘር በቁም፣ በአባላዘር፣ በሽል ወይም በማንኛውም መልኩ) በሚገቡበት ጊዜ በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲሁም ፍተሻ ተደርጎባቸው እንዲገቡ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 9. በቁም፣ በአባላዘር እና በሽል ወደ ሀገር የሚገቡ የእንስሳት ዝርያዎች የዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን 6 የምርመራ (Bovine Tuberculosis, Brucellosis, Bovine viral diarrhea-mucosa disease (BVD-MD), Bovine Venereal Trichomoniasis, Infectious Bovine |

| | |
|---|---|
| | Rhinotrachitis (IBR), and Campylobacter fetus) መስፈርቶች ሊያሟሉ ይገባል፡፡ |
| | 10. የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን በመለየት በሳይንሳዊ ምርምር ውጤት እንዲያገኙ አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 11. ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት የሚውል የመኖ ፍጆታና ሌሎች ግብአቶች አይነትና መጠን በዕቅድ ተይዞ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 12. በዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ለእንስሳቱ የአመጋገብ ቀመር በማውጣት በወጣው ቀመር መሰረት የተመገቡ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 13. በእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች የተከናወኑ ማሻሻያ ሥራዎች የተሟላ መረጃዎች የሚያዙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 14. የተከናወኑ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች ተጠናቅረው ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 15. የዝርያ ማሻሻል ሥራ በታቀደው ጊዜና መጠን መሰረት ሊፈጸም ይገባል፡፡ |
| 2. **የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲጠበቁ መደረጉን ማረጋገጥ፤** | 16. ለዝርያ ማሻሻል የሚመረጡ እንስሳት ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 17. በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ውስጥ ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ የእንስሳት ጤና ሁኔታዎች ላይ የስጋት ትንተና በማካሄድና መጠኑን በመለየት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| | 18. የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች በልዩ ክብካቤ፣ ጥብቅ ስፍራዎች ተይዘው እንዲራቡ እንዲጠበቁና ጥቅም እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 19. ነባር የእንስሳት ዝርያዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲጠበቁ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 20. ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች በተከሰተባቸው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ቦታዎች (ክልሎች) በመገኘት ስለደረሰው ጉዳት እና መንስኤ ጥናት በማድረግ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 21. ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራ ወደ ሀገር የሚገቡትም ሆነ ከአገር ውስጥ የሚሰበሰቡት እንስሳት ላይ የኳራንቲን አገልግሎት በመስጠት ተላላፊ የእንስሳት በሽታዎችና በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ ተህዋስያን ተጽዕኖዎችን መከላከል ይገባል፡፡ |
| | 22. ከእንስሳት ዝርያ ጋር በተያያዘ የበሽታ ክስተት ሲያጋጥም ለሀገራዊ የመረጃ ቋት መረጃው እንዲያዝ ሊያሳውቁ ይገባል፡፡ |
| | 23. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለተከናወኑ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አጠቃቀምና ጥበቃ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች፣ ቡድኖች፣ የህብረተሰብ ክፍሎች የእውቀትና፣ የክህሎትና የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 24. ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት የሚውል የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻዎችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች የጥገና ፕሮግራም በማዘጋጀት በፕሮግራሙ መሰረት እንዲከናወን ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| **3.የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መባዛታቸውን፣ መሰራጨታቸውን እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረጉን ማረጋገጥ፤** | 25. የእንስሳት የብዜትና የስርጭት ማዕከል በአስፈላጊና በአመቺ አካባቢዎች እንዲቋቋም ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 26. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ለአርብቶ አደሩ፣ ለአርሶ አደሩ እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ሊሰራጩ ይገባል፡፡ |
| | 27. በዝርያ ማሻሻል ሥራ የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነት ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 28. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ማዕከላትን የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 29. ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ የተመረቱ አባላዘሮችን ለማስቀመጥ የሚጠቅም የፈሳሽ ናይትሮጂን ምርት የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 30. አባለዘርና ናይትሮጂን ምርት ለክልል እና ለወረዳዎች እንዲሰራጭ እና አገልግሎት ላይ ስለመዋሉ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 31. የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ለሃገሪቱ |

| | |
|---|---|
| | ተጠቃሚዎችና አግባብነት ላላቸው ዓለም ዓቀፍ ተቋማት የሚተላለፍበትን ስልት በመቀየስ በድህረ ገጽ እንዲሰራጩ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 32. ከዚህ በፊት የተከናወኑ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች መረጃዎች ሊጠናቀሩ፣ ሊገመገሙና ግብረ መልስ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡ |

## አባሪ ሁለት ፡የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር ተቋማዊ ቁመና (Organogram)



## አባሪ ሦስት፡ በየአመቱ ያሉ የእንስሳትን ሞትና የመኖ ፍጆታ

| ዓመተ ምህረት | ነባር የዝርያ እንስሳት | የገቡ | የተወለዱ | ድምር | ውርጃ | የተወገዱ | የሞቱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2005 | 173 | 300 | 5 | | 11 | 1 | 2 |
| 2006 | | - | 11 | | - | 5 | 318 |
| 2007 | | - | 74 | | 31 | 17 | 139 |
| 2008 | | - | 100 | | - | 25 | 165 |
| 2009 1ኛ ሩብ ዓመት | | - | 6 | | 6 | 12 | 45 |
| ድምር | 173 | 300 | 196 | 669 | 48 | 60 | 667 |

***ማስታወሻ***

- ከ2006 ዓ.ም እና 2008 ዓ.ም የውርጃ ህክምና ቢሰጥም ዳታው በትክክል ባለመገለፁ፣ መድኃኒቱ ባለመገዛቱ ፣ ላሞቹ በአይ ቢ አር በሽታ በመያዛቸው የሰውነት መቋቋም ችግርና የውርጃ ዳታው ከ50% በታች መሆኑን ብቻና በቁጥር በትክክል ባለመገለፁ ዳታ ውስጥ ለማስቀመጥ አልተቻለም፡፡
- የሞቱት ቁጥር ከ2005 ዓ.ም ውጭ ያሉት ነባሮቹን እና አዲስ የተወለዱትን ይጨምራል፡፡

## አባሪ አራት፡

**በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ወላይታ ዞን እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ በዓመት ውስጥ ለማቅረብ የታቀደ፣ የቀረበ እና ጥቅም ላይ የዋለ አባላዘር ብዛት፡-**

| | በዓመቱ ውስጥ ለማቅረብ የታቀደ አባላዘር ብዛት በዶዝ | በዓመቱ ውስጥ የቀረበ አባላዘር ብዛት በዶዝ | ጥቅም ላይ የዋለ የአባላዘር ብዛት በዶዝ | ጥቅም ላይ ያልዋለ የአባላዘር ብዛት በዶዝ | የዓመቱ ክንውን ከዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2006 ዓ.ም | 34,038 | 28,790 | 26,790 | 2,000 | 85 |
| 2007 ዓ.ም | 25,250 | 26,696 | 20,901 | 5,795 | 106 |
| 2008 ዓ.ም | 38,438 | 34,627 | 32,204 | 2,423 | 90.1 |
| ድምር | 97,726 | 90,113 | 79,895 | 10,218 | |

Office of the Federal Auditor General

# አባሪ አምስት

**በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ በድራት ማጎልበቻ (ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ ላሞች**

| | ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ ላሞች ለማዳቀል የተያዘ ዕቅድ | ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ የተከናወነባቸው ላሞች ብዛት (ክንውን) | ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ በኋላ የተወለዱ የጥጃና የጊደር ብዛት | የዓመቱ ክንውን ከዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2006 ዓ.ም | 50,496 | 45,837 | 16,536 | 90.8 |
| 2007 ዓ.ም | 306,000 | 193,533 | 55,364 | 63.2 |
| 2008 ዓ.ም | 315,000 | 80,661 | - | 25.6 |
| ድምር | 671,496 | 320,031 | 71,900 | |

**በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ በድራት ማጎልበቻ (ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ ላሞች**

| | ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ ላሞች ለማዳቀል የተያዘ ዕቅድ | ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ የተከናወነባቸው ላሞች ብዛት (ክንውን) | ሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ በኋላ የተወለዱ የጥጃና የጊደር ብዛት | የዓመቱ ክንውን ከዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2006 ዓ.ም | 70,000 | 35,257 | 11,732 | 50.4 |
| 2007 ዓ.ም | 55,000 | 59,057 | 15,528 | 107.4 |
| 2008 ዓ.ም | 69,750 | 63,635 | 20,335 | 91.2 |
| ድምር | 194,750 | 157,949 | 47,595 | |

# አባሪ ስድሰት

## በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ የፈሳሽ ናይትሮጂን የጥገና ወጪ

| ተ.ቁ | የማዕከሉ ስም | በጀት ዓመት | በማዕከሉ የተገዛ | በክልል የተገዛ | ጠቅላላ ወጪ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፍቼ | 2006 | 324.94 | 403,650.00 | 403,974.94 |
| | ሻሸመኔ | 2006 | 0 | 0 | 0 |
| | ነቀምቴ | 2006 | 73,928.00 | 545,457.60 | 619,385.60 |
| | | | 74,252.94 | 949,107.6 | 1,023,360.54 |
| 2 | ፍቼ | 2007 | 178,978.83 | 112,700.00 | 291,678.83 |
| | ሻሸመኔ | 2007 | 46,000.00 | 0 | 46,000.00 |
| | ነቀምቴ | 2007 | 93,000.00 | 0 | 93,000.00 |
| | | | 317,978.83 | 112,700.00 | 430,678.83 |
| 3 | ፍቼ | 2008 | 278,542.00 | 396,478.25 | 675,020.25 |
| | ሻሸመኔ | 2008 | 324,999.99 | 467,000.00 | 791,999.99 |
| | ነቀምቴ | 2008 | 14,800.00 | 0 | 14,800.00 |
| | | | 618,341.99 | 863,478.25 | 1,481,820.24 |
| | ጠቅላላ ድምር | | 1,010,573.76 | 1,925,285.85 | 2,935,859.61 |

## በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ የፈሳሽ ናይትሮጂን የጥገና ወጪ

| ዓ.ም | ጠቅላላ ወጪ |
|---|---|
| 2006 | - |
| 2007 | - |
| 2008 | 6,370,175.99 |

# አባሪ 7፡ በናሙና የታዩ ቦታዎች፣ ማዕከላትና ቢሮዎች

| በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | | | |
|---|---|---|---|
| | | መጠይቅ የቀረበላቸው የሥራ ሃላፊዎች | መጠይቁ የቀረበበት ቀን |
| 1 | ሆለታ አስኳል መንጋ አስተዳደር | የሆለታ አስኳል መንጋ አስተዳደር ዝርያ ማሻሻያ ኬዝ ቲም አስተባባሪ | 02/09/08<br>16/02/09 |
| 2 | ሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል | ብሄራዊ የወተት ከብቶች ኮሞዲቲ ምርምር አስተባባሪ | 18/02/09 |
| 3 | ኦሮሚያ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ቢሮ | የወተት ልማት ባለሙያ | 07/02/09 |
| 4 | የወልመራ ወረዳ የእንስሳት ዕርባታና ዓሳ ልማት ቢሮ | ምክትል ኃላፊና የእንስሳት ዕርባታና ዓሳ ልማት ስራ ሂደት መሪ | 18/02/09 |
| 5 | ለአርሲ ዩኒቨርስቲ የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከል | የግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ ዲን | 19/03/09 |
| 6 | አሰላ ቀጠና እንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪ | ኃላፊ | 19/03/09 |
| 7 | በአርሲ ዞን እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ | የእንስሳትና ዓሳ ሀብት አርሲ ዞን ኃላፊ | 19/03/09 |
| በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | | | |
| 8 | ወላይታ ሶዶ እርባታ ማዕከል | የማዕከሉ ተወካይ | 21/03/09 |
| 9 | ወላይታ ሶዶ የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከል | የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር | 21/03/09 |
| 10 | ደቡብ ክልል እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ | የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ ኃላፊ | 29/03/09 |
| 11 | ሐዋሳ አባላዘር ማምረቻ ማዕከል ጽ/ቤት | የዝርያ ማሻሻል ክትትልና ግምገማ ባለሙያ | 23/03/09 |
| 12 | ደቡብ ክልል እንስሳትና ዓሳ ሀብት ቢሮ የአዳቃይ ቴክኒሺያን ስልጠና ክፍል | የዳልጋ ከብት ዝርያና ምርት ማሻሻያ ባለሙያ | 28/03/09 |
| 13 | ሐዋሳ ፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከል | የእንስሳት ዝርያ ብዜት ባለሙያ<br>የእንስሳትና ዓሳ ግብዓት ባለሙያ | 23/03/09<br>28/03/09 |